በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

??/? /?? ? 203381
?? 30/3/2014 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - 1. አቶ ጌታቸው ዳንደና 2. ወ/ሮ ቅዱስት ቢያዝን

ከጠበቃ- ካሌብ አለባቸው ጋር ቀርበዋል

ተጠሪ - አቶ አልዓዛር ዳዊት

ከጠበቃ ደሳለኝ ደምሴ ጋር ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካቾች የካቲት 25 ቀን 2013 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 758936 የካቲት 17 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 48597 መጋቢት 2 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ማብራሪያ ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ቅሬታቸውን በማቅረባቸው ነው፡፡ ቅሬታቸውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካቾች የሚቃወሙባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልን ይገባል የሚሉትን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤቶች ሟች ከተናዘዙችው ኑዛዜ ውጪ የውርስ ንብረት ለተጠሪ እንዲሰጥ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ መጀመሪያ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ እርማት በሚል አዲስ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ሟች ወ/ሮ ዓለም ፀሀይ እያሱ በ29/6/1992 ዓ/ም ኑዛዜ አድርጋለች፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከሳሽና ተከሳሾች ካርታ በጋራ ለማውጣት ስንስማማ አብላጫ ድርሻዬን ለመልቀቅ አልተስማማሁም፡፡ በመሆኑም በኑዛዜው መሰረት ክፍፍል እንዲደረግልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ተከሳሾችም ሟች ለከሳሽና ተከሳሾች ኑዛዜ አድርጋለች፡፡ ይሁንና ከሳሽና ተከሳሾች በ7/7/1997 ዓ/ም ባደረግነው የውል ስምምነት ለከሳሽ የአብላጫ ድርሻ የተደረገለት ቢሆንም ሁላችንም እኩል እንድንካፈል የተስማማን በመሆኑ እኩል አንድንካፈል በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 48597 ግንቦት 9 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ሟች ወ/ሮ አለም ፀሀይ ኑዛዜ ያደረገች መሆኑ አልተካደም፡፡ በ7/7/1997 ዓ/ም በከሳሽና ተከሳሾች መካከል ተደረገ የሚባለው ውል ቤቱን በስማቸው በሶስቱም ስም ለማስመዝገብ የተስማሙና በውሉ ላይ "የቤቱ አብላጫ የኔ ቢሆንም…" የሚል ቃል ሲታይ ድርሻውን ትቷል የሚል ሀሳብ የሚያመለክት ባለመሆኑ ከሳሽና ተከሳሾች በኑዛዜው መሰረት ይካፈሉ ሲል የክፍፍሉን ዓይነት ዘርዝሮ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚሁ መዝገብ መጋቢት 2 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት ከአፈጻጸም ችሎት ማብራሪያ ተጠይቄያለሁ በሚል የማብራሪያ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተከሳሾች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚሁ መዝገብ መጋቢት 2 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው የማብራሪያ ትእዛዝ ላይ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው በመ/ቁጥር 758936 የካቲት 17 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኛቸውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካቾችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 48597 ግንቦት 9 ቀን 2009 ዓ/ም በተሰጠው ውሳኔ "በተደረገው ኑዛዜ መሰረት ንብረቶቹ ላይ ለውጥ የተደረገበት ቢሆንም አሁን ባለበት ሁኔታ ተለይቶ እና ተለክቶ ለአመልካቾች ተከፍሎ ይሰጥ" የሚል ሲሆን ውሳኔውም በተጠሪ አመልካችነት እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ፀንቶ ባለበት በተጠቀሰው መዝገብ ላይ በመጋቢት 2 ቀን 2012 ዓ/ም በተሰጠው የማብራሪያ ትእዛዝ ለአመልካቾች ከተሰጡ ቤቶች ውጪ ያሉ በቤት ቁጥር 068 ሥር የሚጠቃለሉ ናቸው በሚል የተወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሚያዝያ 12 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካቾችም ግንቦት 4 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ሟች ወ/ሮ ዓለም ፀሀይ እያሱ በ29/6/1992 ዓ/ም ባደረገችው ኑዛዜ መሰረት የውርስ ንብረቱ ክፍፍል ይደረግልን ሲል ጠይቆ የአሁን አመልካቾችም መልስ ሰጥተውበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 48597 ግንቦት 9 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የሟች የውርስ ንብረቶች ሟች በ29/6/1992 ዓ/ም ባደረገችው ኑዛዜ መሰረት እንዲፈጸም ይሄውም 1. በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 08 ቀበሌ25 የቤት ቁጥር 068 ከሆነው ቤት ጋር ተጠቃሎ የሚገኘውን እና አሁን ደግሞ በእነ አላዛር ዳዊት ስም በተዘጋጀው በቤት ካርታ ውስጥ የሚገኘውን በኑዛዜ አገላለጽ በወቅቱ የእቃ መሸጫ ሱቅ ተብሎ የተለየውን ቤት ከኑዛዜ በኋላ በዚህ ቤት ላይ ለውጥ የተደረገበትም ቢሆንም አሁን ባለበት ሁኔታ ተለክቶ ለወ/ሮ ቅድስት ቢያዝን ተከፍሎ እንዲሰጥ፡፡ 2. በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 08 ቀበሌ 25 የቤት ቁጥር 068 ከሆነው ቤት ጋር ተጠቃሎ

የሚገኘውን እና አሁን ደግሞ በእነ አላዛር ዳዊት ስም በተዘጋጀው በቤት ካርታ ውስጥ ተጠቃሎ የሚገኘውን በኑዛዜ አገላለጽ በወቅቱ አቶ ጌታቸው ዳንደና ምግብ ቤት አድርጎ ይነግድበት የነበረውን ምግብ ቤት ተብሎ የተለየውን ቤት ከኑዛዜው በኋላ በዚህ ምግብ ቤት በነበረው ቤት ላይ የተደረገ ለውጥ ቢኖርም አሁን ባለበት ሁኔታ ተለይቶ እና ተለክቶ ለአቶ ጌታቸው ዳንደና ተከፍሎ እንዲሰጥ፡፡ 3. ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ ለወ/ሮ ቅድስት ቢያዝን እና ለአቶ ጌታቸው ዳንደና የተወሰነላቸው ሱቅና ምግብ ቤት ለተጠሪዎች ከተሰጠ በኋላ የሚቀረውን በአ/አበባ ከተማ ወረዳ 8 ቀበሌ 25 የቤት ቁጥር 068 የሆነው ቤት እና በአሁኑ ሰዓት ደግሞ በእነ አላዛር ዳዊት ስም በተዘጋጀው ካርታ የሚታወቀው ዋና መኖሪያ ቤት ከነ ከፍት ይዞታዎቹ ከሌሎቹ ወራሾች በአብላጫነት ተከፍሎ ለአቶ አላዛር ዳዊት እንዲሰጥ ሲል ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በግልጽ እንደሚያመለክተው ለአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች የውርስ ንብረት ክፍፍሉ ለወ/ሮ ቅድስት ቢያዝን የእቃ መሸጫ ሱቅ የነበረው ከኑዛዜ በኋላ በዚህ ቤት ላይ ለውጥ የተደረገበትም ቢሆንም አሁን ባለበት ሁኔታ እንዲሰጣት የሚልና ለአቶ ጌታቸው ዳንደና ምግብ ቤት የነበረው ከኑዛዜው በኋላ በዚህ ምግብ ቤት ላይ የተደረገ ለውጥ ቢኖርም አሁን ባለበት ሁኔታ እንዲሰጠው የሚል ነው፡፡ በመሆኑም የፍርድ አፈጻጸም ችሎቱ ለአሁን አመልካቾች እንዲሰጣቸው የተባሉት ቤቶች ላይ ከኑዛዜ በኋላም በነዚህ ቤቶች ላይ የተደረገ ለውጥ ቢኖር አሁን ባለበት ሁኔታ የተወሰነላቸው በመሆኑ ከዚሁ ውሳኔ አንጻር አይቶ ማስፈጸም ሲቻል ማብራሪያ በሚል ምክንያት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቤቶቹን ኑዛዜውን መሰረት በማድረግ በካሬ ሜትር ለይቶ የሰጠው አዲስ ውሳኔ ከሥነ ሥረዓት ህጉ ውጪ የራሱን ውሳኔ በመለወጥ የተሰጠ ውሳኔ የሚሆን ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 373 (2) እንደ ፍርድ እንዲያስፈጽም ትእዛዝ የተላለፈለት ፍርድ ቤት የተላለፈለትን ጽሁፎች በአንድ መዝገብ ውስጥ ይዞ ስለ ፍርዱ ትክክለኛነት ወይም በግልባጮቸ ላይ ስለ ሰፈረው ነገር ሌላ መግለጫና ማብራሪያ ሳይጠይቅ በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ማስፈጸም አለበት፡፡ ስለሆነም የፍርዱን ወይም የትእዛዙን ወይም የግልባጩን ትክክለኛነት የሚያጠራጥር ልዩና በቂ ምክንያት ያጋጠመው እንደሆነ ይህንኑ መዝግቦ ማረጋገጫ የሚሆን ማስረጃ እንዲላክለት ለመጠየቅ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 48597 ግንቦት 9 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው፣ በኑዛዜው መሰረት ውሳኔ አልተሰጠኝም የሚል ወገን ወይም ውሳኔው ግልጽ ያልሆነና የማይፈጸም ነው የሚል ወገን ካለ ቅሬታውን በይግባኝ ለሚያየው ፍ/ቤት አቅርቦ ማሳረም እንጂ በማብራሪያ መክንያት መጀመሪያ ከተሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ መስጠት የሥነ ሥረዓት ህጉ የማይፈቅድና ህጋዊ መሰረትም የሌለው ነው፡፡ በሌላ በኩል በዚህ ጉዳይ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 48597 ግንቦት 9 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካቾችና የአሁን ተጠሪ ቅሬታ አቅርበውበት እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይም ነው፡፡ የአሁን ተጠሪም በዚሁ ማብራሪያ ተብሎ ውሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ የማብራሪያ ትእዛዝ ሳይሰጥበት በፊት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦበት እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ውሳኔ ያገኘ ሲሆን ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ እንደገና በማብራሪያ ምክንያት አዲስ ውሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 758936 የካቲት 17 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 48597 መጋቢት 2 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ማብራሪያ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት መጋቢት 17 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ኮ/ቀ/ም/ችሎት የመ/ቁጥር 76038 ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም